የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Regional Integration

# <u>መመሪያ ቁጥር 940/2015</u>

## የሲሚንቶ ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 940/2015

በሀገራችን የግንባታ ዘርፍ ማደግን ተከትሎ የሲሚንቶ ገበያ በተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ በመምጣቱ ሥርጭቱ እየተስተጓጎለ እና የዋጋ ንረቱ እየተባባሰ በመምጣቱ የሲሚንቶ ገበያውን ለማረጋጋት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭትን አስመልክቶ ያወጣው የአሠራር መመሪያ ቁጥር 908/2014 በተግባር ሲፈተሽ ሲሚንቶን በቀጥታ ከፋብሪካው የመግዛት እድል ያገኙ አካላትና ተጠቃሚዎች በዋጋም ሆነ በአቅርቦት ተጠቃሚ መሆን የቻሉ ቢሆንም በተመረጡ አቅራቢዎች ለህብረተሰቡ እንዲደርስ የተደረገው የሲሚንቶ ሥርጭት የተጠቃሚውን ፍላጎት ያላሟላ ከመሆኑም በላይ ለተለያዩ ህገወጥ አሠራሮች የተጋለጠ መሆኑን በመገንዘብ፤

በአሁኑ ወቅት ሥራ ላይ ያለው የሲሚንቶ የሥርጭት ሥርዓት አፈፃፀሙ በርካታ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ የተሻለ መፍትሄ እንዲበጅ ከህብረተሰቡና ከተለያዩ አካላት የቀረቡ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን በግብዓትነት በመውሰድ፤

በሚኒስቴር መሥሪያቤቱ በኩል በተካሄደው የአፈፃፀም ፍተሻ ጥናት በተለዩ ችግሮችና የመፍትሄ ሐሳቦች ላይ በሲሚንቶ ዘርፍ ከተሰማሩት ባለሀብቶችና ከሚመለከታቸው የክልሎችና የከተማ አስተዳደር የሥራ ሃላፊዎች ጋር በተደረገው ውይይትም ሥራ ላይ ያለውን አሠራር ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን በመግባባት፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 19 (4) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **የሲሚንቶ ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ** ቁጥር 940/2015“ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ሚኒስቴር“** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤
2) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
3) **“የሲሚንቶ ጅምላ ነጋዴ“** ማለት የሲሚንቶ ምርቶችን ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ ወይም መንግስታዊ እና መንግስታዊ ሳልሆኑ ተቋማት ወይም ለህብረት ሥራ ማህበራት በጅምላ የመሸጥ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው ማንኛውም ሰው ነው፤
4) **"የሲሚንቶ ቸርቻሪ ነጋዴ"** ማለት የሲሚንቶ ምርትን ከአምራች፣ ከአስመጭ ወይም ከጅምላ ነጋዴ በመግዛት ለተጠቃሚ የመሸጥ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው ማንኛውም ሰው ነው፤
5) **“የሲሚንቶ አምራች“** ማለት የሲሚንቶ ምርትን በፋብሪካ የሚያመርትና ለገበያ የሚያቀርብ ወይም ለሽያጭ ዓላማ የሚያመርት ማንኛውም ሰው ነው፤
6) **“መጋዘን“** ማለት በፋብሪካዎችና በአካባቢው ንግድን ለማስተዳደር ስልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ የታወቀና ሲሚንቶን ለማከማቸት፣ ለማከፋፈል እና ለመቸርቸር የተዘጋጀ የማከማቻ ህጋዊ ፍቃድ የወጣበት ቦታ ነው፤
7) **“ድርጅት“** ማለት ሲሚንቶን ለግንባታ ዓላማ የሚጠቀም የህግ ሰውነት ያለው ማንኛውም መንግስታዊ፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ አካል ነው፤
8) **“የመንግስት ፕሮጀክቶች“** ማለት በፌዴራልና በክልል መንግስታት በጀት የሚገነቡ ግንባታዎች ናቸው፤
9) **"ሰው"** ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
10) በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ሲሚንቶን በሀገር ውስጥ በሚያመርት፣ ከውጪ ወደ ሀገር በሚያስገባ፣ በጅምላ ወይም በችርቻሮ በሚሸጥ፣ እና ለግንባታ በሚጠቀም ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### ክፍል ሁለት

### ስለ ሲሚንቶ የግብይት ሥርዓት

## 4. የሲሚንቶ የግብይት አሠራር

1) የፌዴራልና የክልል የመንግስት ፕሮጀክት ገንቢና የስራ ተቋራጭ ከአሠሪ መ/ቤት ጋር የተገቡትንና በአስሪው መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተረጋገጠ የሥራ ውል ለፋብሪካው በማቅረብና እንዲሁም ትላልቅ ሪል ስቴት ገንቢና ኦፒሲ ሲሚንቶን በሚጠቀም በሚክሰር የተዘጋጀ ኮንክሪት የሚያመረት ድርጅት ከፋብሪካው ጋር የግዥና የሽያጭ ውል በመዋዋል በቀጥታ ከፋብሪካው ግዥ መፈፀም ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራልና የክልል የመንግስት ፕሮጀክት ገንቢ ሲሚንቶን በአቅራቢያው ከሚገኘው ጅምላ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ መግዛት ይችላል፤
3) የሲሚንቶ ፋብሪካው በዚህ መመሪያ መሠረት ምርቱን በጅምላና በችርቻሮ ከሚያከፋፍል ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ካለው ነጋዴ ጋር ውል በመግባት ሲሚንቶ ለገበያ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡
4) በሲሚንቶ አምራች፤ በጅምላ ነጋዴ፤ በድርጅት እና በቸርቻሪ መካከል የሚደረገው ውል የሲሚንቶ መግዣና መሸጫ ዋጋን ማካተት አለበት፡
5) የሲሚንቶ ፋብሪካ እንዳስፈላጊነቱ በዋና ዋና ከተሞች የማከፋፈያ መጋዝን ማደራጀትና ከፋብሪካ ጭምር በቀጥታ ለተጠቃሚው ሲሚንቶ መሸጥ ይችላል፡፡
6) የሲሚንቶ ፋብሪካ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የፋብሪካ መጋዘን የሲሚንቶ የመሸጫ ዋጋ መሰረት ሽያጭ ይፈጽማል፡፡
7) የሲሚንቶ ፋብሪካ ከፋብሪካው መጋዝን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ መነሻ በማድረግ የትራንስፖርት ወጪ፣ የጫኝና አውራጅ፤ የትርፍ ህዳግና ሌሎች ወጪዎችን ታሳቢ ያደረገ የዋና ዋና ከተሞች የጅምላና የችርቻሮ የመሸጫ ዋጋ ጣሪያ በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያሳውቃል፡፡
8) በፋብሪካ፤ በጅምላና በቸርቻሪ ነጋዴ መካከል የሚፈፀመው ግብይት የገዥውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ባካተተ ህጋዊ ደረሰኝ መሠረት የሚከናወን መሆን አለበት፡፡
9) ሕጋዊና ነፃ የሲሚንቶ ግብይትና ዝውውርን የሚገድቡ አሠራሮችና ኬላዎች መኖር የለባቸውም፤

### ክፍል ሦስት

### የሚኒስቴሩና በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባርና ኃላፊነት

## 5. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የሲሚንቶ ምርት አቅርቦትን መነሻ ያደረገ እንደአስፈላጊነቱ የግብይት እና የስርጭት የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
2. የፋብሪካ መጋዝን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ እንደየአስፈላጊነቱ በየስድስት ወሩ እየወሰነ ያሳውቃል፤
3. ፋብሪካ የፋብሪካውን መጋዝን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ መነሻ በማድረግ ለየከተሞቹ የጅምላና የችርቻሮ የመሸጫ ዋጋ ጣሪያ ማውጣቱን ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው ያሳውቃል፤
4. የሲሚንቶ ግብይት በወጣው ዋጋ መሠረት እየተፈፀመ መሆኑን ይከታተላል፤
5. የሲሚንቶ ምርት አፈፃፀም፣ የስርጭትና የመሸጫ ዋጋ መረጃዎችን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ ይሠጣል፤
6. በዚህ መመሪያ የተቀመጡት አሰራሮች በተገቢው ስለመፈጸማቸው ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡

**6. የክልል እና የከተማ መስተዳደር የንግድ ተቆጣጣሪ አካላት ተግባርና ኃላፊነት**

በክልል እና በከተማ መስተዳድር ንግድን ለመቆጣጠር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ወይም በከተማው ሲሚንቶን በጅምላና በችርቻሮ የሚሸጥ ነጋዴ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤
2) በክልሉ ወይም በከተማው የተለያዩ አካባቢ በየወቅቱ ያለውን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ ይከታተላል፤ ለከተማው በተቀመጠው የዋጋ ጣሪያ መሠረት እየተፈፀመ መኖሩን ይከታተላል፤ ከጣሪያው በላይ ሆኖ ሲገኝ እርምጃ ይወስዳል፤ ለሚንስቴሩም ያሳውቃል፤
3) በክልሉ ወይም በከተማው የሲሚንቶ ነፃ ዝውውርን የሚገድብ አሰራርና ኬላ እንዳይኖር ያደርጋል፤
4) በክልሉ ወይም በከተማው የጅምላ አከፋፋይ እና ቸርቻሪ ነጋዴ ሸያጩን በህጋዊ ደረሰኝ ብቻ ስለማከናዎኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

## ክፍል አራት

## የሲሚንቶ አምራች ፋብሪካ፣ ጅምላና ቸርቻሪ ነጋዴ ግዴታ

**7. የሲሚንቶ አምራች ፋብሪካ ግዴታ**

እያንዳንዱ የሲሚንቶ አምራች ፋብሪካ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1) በፋብሪካው የተመረተ ሲሚንቶን በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 በተደነገገው አግባብ ለነጋዴ እና ለተጠቃሚ ሽያጭ ይፈፅማል፤

2) በፋብሪካው የተመረጠና ሲሚንቶን በጅምላና በችርቻሮ የሚሸጥ ነጋዴ በዚህ መመሪያ መሰረት መፈጸሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤

3) የፋብሪካ መጋዝን የሲሚንቶ ዋጋን መነሻ በማድረግና የትራንስፖርት ክፍያ፤ የጫኝና አውራጅ፤ የመጋዘን ኪራይ ወጪዎችንና የትርፍ ህዳግ በማካተት የሲሚንቶ ምርት በተለያዩ ክልሎችና ከተሞች በጅምላና በችርቻሮ የሚሸጥበትን የዋጋ ጣሪያ በማዘጋጀት ለሚንስቴሩ ያሳውቃል፤

4) የሲሚንቶ ፋብሪካ እንዳስፈላጊነቱ በየስድስት ወሩ_የፋብሪካ መጋዝን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ ክለሳ እንዲደረግ በጥናት የተደገፈ ጥያቄ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፤

5) በፋብሪካው፤በጅምላ አከፋፋይ፤ በቸርቸሪዎች፤ እና በድርጅቶች መካከል የሚገባው የግብይት ውል በዚህ መመሪያ ተደነገጉትን ግዴታዎች የያዘ እንዲሆን ያደረጋል፤ ለዚህ የሚሆን የውል ፎርማት በማዘጋጀት ለጅምላ አከፋፋይና ቸርቸሪዎች እንዲደርስ በማድረግ ያስፈፅማል፤

6) የሲሚንቶ አምራች ፋብሪካ የሲሚንቶ ግዥና ሽያጭ እንቅስቃሴቸውን የሚያሳይ መረጃ በአግባቡ የመያዝ፣ በተቆጣጣሪ አካላትም ሲጠየቁ የማቅረብ ግዴታ አለበት፣

7) የፋብሪካውን የምርት መጠንና የሥርጭት አፈፃፀም (ለመንግስት ፕሮጀክት፤ ለጅምላ ነጋዴ፣ ለቸርቻሪ እና ለሌላ ተጠቃሚ የተፈፀመውን ሽያጭ) እንዲሁም ከሥርጭት ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ ችግሮችንና የመፍትሄ ሐሳቦችን በተመለከተ ለሚኒስቴሩ በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

**8. የሲሚንቶ ጅምላና ቸርቻሪ ነጋዴዎች ግዴታ**

እያንዳንዱ የሲሚንቶ ጅምላና ቸርቻሪ ነጋዴ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1) የሲሚንቶ ግብይቱን በዚህ መመሪያ መሠረት ያከናውናል፤

2) የሲሚንቶ ጅምላ ነጋዴ ሲሚንቶ የሚገዛውን ቸርቻሪ ድርጅት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በመመዝገብ በህጋዊ ደረሰኝ ሽያጭ ማከናወን አለበት፤

3) በግዥ የተረከበውን ሲሚንቶ በተቀመጠው የዋጋ ጣሪያ መሠረት ለማንኛውም ተጠቃሚ መሸጥ አለበት፤ ሲሚንቶን ከህጋዊ መስመር ውጭ አሳግባብ አከማችቶ መያዝና ከተተመነው የዋጋ ጣሪያ በላይ መሸጥ አግባብ ባለው ህግ ያስጠይቃል፤

4) የሲሚንቶ ቸርቻሪ ነጋዴ የያዘውን የሲሚንቶ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በንግድ መደብሩ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት፤

5) የሲሚንቶ ግዥና ሽያጭ እንቅስቃሴውን መረጃ በአግባቡ የመያዝ፣ በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ

ይህን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 10. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመርያ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 11. የተሻሩ መመሪያዎች እና አሰራሮች

የሲሚንቶ አቅርቦትና ግብይት መመሪያ ቁጥር 908/2014 እና የስሚንቶ ግብይትና ዝውውርን አስመልክቶ መስከረም 6 ቀን 2015 ዓ.ም. የወጣው የህዝብ ማስታወቂያ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

### 12. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ይህንን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

### 13. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ገብረመስቀል ጫላ ሞጣሎ**

**የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር**
**ታህሳስ 27/2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**